ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

**ዴሞ ቅጽ** 33 **ቁ.** 9 **ሰኔ** 2000 **ዓ.ም.**

# ራዕይ ያጣ ትግል አቸናፊ አይሆንም

***የኢትዮጵያ ብሔራዊ ትግል ከማንኛውም ጉዳይ በቅድሚያ አንግቦ ሊራመድ የሚገባው ተግባር÷ ከአድማስ ባሻገር የሚያይ ራዕይ ሊሆን ይገባው ነበር:: ይህ ሆኗል ብሎ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያምን አይደለም:: የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች ከየግል ድርጅቶቻቸው የፖለቲካ ፕሮግራማቸው አልፈው ተርፈው÷ በጋራ ብሔራዊ አጀንዳና ራዕይ ዙሪያ ተሰባስበው የሀገራቸውን መሠረታዊ ችግሮች በጋራ ተወያይተው ብሔራዊ መፍትሔ ሊያገኙ ቢጥሩም አልቻሉም:: ይህም በመሆኑ እስከዛሬ ድረስ ወያኔን ለማስወገድ የሚያስችላቸውን መጨረሻ ድልን የሚያረጋግጥ የጋራ ሙያ ሊፈጽሙ አልተሳካላቸውም:: ኅብረት ለመፍጠር የተደረጉት ሙከራዎቻቸውም ሀገሪቷና ዜጎቿ የጓጉትን ውጤት አስመዝግበው÷ ሀገሪቱን ከዘረኞቹ አምባገነን ሥርዓት ሊያላቅቁ አልተቻላቸውም::***

***ኢትዮጵያ ሰፊ ሀገር ነች:: ዜጎቿም÷ ብዙና ልዩ ልዩ ባኅሎች÷ ቋንቋዎችና ዕምነቶች÷ ያሏቸው ናቸው:: ይህ ግን በጋራ ሀገራቸውና ታሪካቸው÷ በጋራ ችግራቸውና የወደፊቱም የጋራ ራዕያቸውና ዕድላቸው ውስጥ የተካተተ ነው:: የጋራ ራዕይና ተስፋ÷ ሀገርና ዕድል ለአለው ሕዝብ ደግሞ የጋራ ችግሩን ለማስወገድ በጋራ ራዕይ ላይ የተመሠረተ ትግል ማካሄድ ወሳኝነት አለው:: በዕርግጥም የተቃዋሚ ድርጅቶች ነን የሚሉት÷ መሆናቸውን ከልብ የሚያምኑበት ከሆነ÷ ከሚያለያያቸው ይልቅ በአንድ ሀገራዊ ራዕይና ብሔራዊ አጀንዳ ዙሪያ ሊያሰልፋቸው የሚችለው ጉዳይ ሚዛኑ የከበደና የላቀ ነበር፤ ነውም:: ሚዛኑ የከበደ÷ መጨረሻ ግቡም የሀገር ጉዳይ ነው ከተባለና ከታመነበትም÷ ዕምነትን ወደ ተግባር ለመለወጥ የማይቻልበት አሳማኝ ምክንያት ሊኖር አይችልም:: ዕምነትን ወደ ተግባር ለማስለወጥ የሚያስችል ዕምነት ከሌለ ደግሞ መጀመሪያውኑም ቢሆን ዕምነት የሚባል ነገር የለም ማለት ነው:: ወይም ደግሞ ከጥንቱ ከጧቱ አንስቶ የዕምነትን ትክክለኛ ትርጉም መረዳት አልተቻለም ማለት ነው:: ሀገርን እወዳለሁ ሕዝብንም አፈቅራለሁ ተብሎ ከታመነበትና ዕምነትን ከዓላማ÷ ዓላማን ከተግባር ጋር በማዋሃድ መታገል ከተፈለገ÷ ከአድማስ ባሻገር ዘልቆ ለማየት የሚያስችል ራዕይ እንዲኖር ግድ ይላል:: ይህንን መረዳት ቢቻል ኖሮ÷ተቃዋሚ ድርጅቶች ሁሉ ፀሀይ በበረቀ ጀንበር በጠለቀ ቁጥር የአቋምና የዕምነት መለዋወጥና መገለባበጥ ባላሳዩም ነበር:: ይህም በመሆኑ ጥራት ያለው የአጀንዳ ማለትም የዓላማና የተግባር ቅደም ተከተል ሊኖር አልተቻለም:: የጋራ ብሔራዊ አጀንዳ***

ከሌለ ደግሞ የጋራ ራዕይ ይኖራል ተብሎ አይጠበቅም። በተቃዋሚው ጎራ ያለው ዓይነተኛው ችግር አንዱ፥ ይህ ነው።

የሀገራችንን ዘርፈ ብዙ ችግር ለመፍታት የሚቻለው፥ ስፋትንና ጥልቀትን በአነገበ ራዕይ እየተመሩ ፀንቶ በመታገል የሥርዓት ለውጥ ማምጣት ሲቻል ነው። የሥርዓት ለውጥና ጥገናዊ ለውጥ የሰማይና የምድርን ያህል ልዩነት ስላላቸው፥ እነርሱን በሚገባ በመለየት የሥርዓት ለውጥ መምጣት አለበት ብለው የሚያምኑ ኃይሎች ሁሉ በአንድ ጎራ ተሰልፈው በአንድ የጋራ ብሔራዊ ራዕይ ዙሪያ ተሰብሰብው ቢታገሉ የአመረቃ ውጤት ሊያስመዘግቡ ይችላሉ። በጥገናዊ ለውጥ የሀገራችንን ችግር መፍታት አለብን የሚሉ ክፍሎች ደግሞ ምርጫቸው ስለሆነ፥ የሥርዓቱ አካልና አምሳል በመሆን የሥርዓቱ አራማጆች በሚፈቅዱላቸው ችሮታ ዕድላቸውን መፈተን የግድ ይሆንባቸዋል። የእናት ሆድ ዥንጉርጉር እንደሚባለው፥ ለአንድ ሀገር ሕዝብ እንታገላለን የሚሉም ሁሉ እንደ የዕምነታቸው የየግላቸውን የተለያየ የትግል ስልት ቢመርጡ የሚያስደንቅ አይሆንም። ችግር ሊፈጠር የሚችለው ግን፥ በዓላማቸው ፀንተው ለሥርዓት ለውጥ የሚታገሉትን ኃይሎች ለማደናቀፍ፥ ለመከፋፈልና አልፎ ተርፎም ለአምባገነን ሥርዓት አራማጆች ሊያቀራርባቸው ይችላል ብለው በሚገምቱት ሰበብ የእጅ መንሻ ለማድረግ ሲጣጣሩ ነው። ይህ ሊፈቀድላቸው አይገባም።እንደየ አመጣጣቸውና አካሄዳቸው እያሳፈሩ መስደድ ይገባል። በዓላማቸው ጸንተው ወያኔን በሚታገሉና ነፃነታቸውንም ጠብቀው በዕምነታቸው ፍንክች ሊሉ በማይችሉ ድርጅቶች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት፥ እናጥፋቸው የሚሉ ሀሳዊ መሲሂዎች እንዳሉ የአደባባይ ምሥጢር ከሆነ ቆይቷል። እርስ በርስ እያናቆሩና እያፋጁ ማጥፋት የሚለውን የወያኔ አጀንዳ ተቀብለው ደፋ-ቀና የሚሉ ክፍሎች መኖራቸው ከምን ጊዜውም በበለጠ ዛሬ ገሃድ እየሆነ መምጣቱ አያስደንቅም። የወያኔን ተቀባይነት ለማግኘት፥ ግዳይ ጥሎ መቅረብ የግድ ይላልና የተሰጣቸውን ተልዕኮና ግዳጅ ፈጽመው መገኘት ይኖርባቸዋል። ለአዲሱ ጌታ ታማኝነትን ለመግለጽ ወያኔ ቀንደኛ ጠላቶች ናቸው ብሎ የሚፈራቸውን ኃይሎች በመነጠል አውግዘውና ከቻሉም፥ “አጥፍተው” መሄድ አለባቸው። ይህንን ማድረግ ለታማኝነታችን ማረጋገጫ ይሆንልናል ብለውም ያምናሉ። ከዚህ ቀደምም በተለያዩ ወቅቶች፥ በሚከሰቱ አጋጣሚዎች፥ የታገሉበትን ድርጅት ምሥጢር እያወጡና እየከዱ ወደ ደርግና ወደ ወያኔ የሄዱትን ማስታወሱ ይበቃል። እነኝህ ክፍሎች ምን ዕድል እንደገጠማቸው መዘርዘር አይኖርብንም።

እየታገሉ መዋደቅ፥ እየተዋደቁ በኩራት ማለፍ ደግሞ ለሁሉም የሚታደል ፀጋ ስለአልሆነ፥ ሁሉም እንደ ተግባሩና ባኅርዩ ይታደለዋል። ዕደላው፥ በአንድ በኩል ለታሪክ ኩራት ሲሆን፥ ተፃራሪው ደግሞ ለሀፍረትና ለውርደት ይሆናል። ለሥርዓት ለውጥ የሚታገለው ኃይል ያነገበው ራዕይ ያነጣጠረው፥ በሀገሪቱ መሠረታዊ ችግሮችና እነዚህስ ብሔራዊ ችግሮች በዘለቄታ መልኩ እንዴት መፍትኄ ሊያገኙ ይችላሉ በሚለው ላይ ነው። ይህም ሀገራችን ዝንተ-ዓለሟን በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ምክንያቶች ከሚፈራረቁባት ችግሮች ለአንድየ ለዘለቄታው የምትላቀቅበትን ሁኔታ በሂደት ሊያስገኝላት ይችላል ተብሎ ይታመናል። ለችግሯ መፍትኄ ፍለጋ የመጀመሪያው ምዕራፍ፥ የዴሞክራሲ ሥርዓት መሠረት መጣል መሆኑ ሊያከራክር ከቶ አይችልም። የዲሞክራሲን ሥርዓት መሠረት ለመጣል የሚደረገው ትግል ደግሞ ሀገራዊ ራዕይ ከሌለው፥ በጥገናዊ ለውጥ ብቻ ይወሰንና አያሌ ምዕራፍ ሊያስጉዝ የሚችል ትግል ለማራመድ አያስችልም። ይህ ደግሞ ዞሮ ዞሮ ሀገራችንን ወደ አንድ የልማትና የኢኮኖሚ ዕድገት ሊያራምዳት የሚያስችላትን ዕድል ሁሉ ይዘጋባታል። የተሰለቸው፥ የተጠላውና የተዳከመው አምባገነን እየሄደ አዳዲስ አምባገነኖች እንዲቀፈቅፉ ይጋብዛል፥ ያበረታታል። ይህም በፈንታው በአዲስ መልክ ሀገሪቱን ለመግዛት ለሚያቆበቁቡ አምባገነኖች በር ከፋች ሁኔታዎችን ያመቻችላቸዋል፤ ሰላምና መረጋጋት አይመጣም። ሀገሪቱን ሳልተጠበቀ ምስቅልቅልና ሽብር ሊዳርግ የአጋንንትን በረት ይከፍታል። የኢትዮጵያን ሕዝብ በሙሉ የሚያሳትፍ ሁኔታን አይፈጥርም። ይህ ደግሞ ያው ዞሮ ዞሮ “ይሻልን ሰድጄ ይብስን አመጣሁ” ወደሚለው የሕዝብ ዘለዓለማዊ ስቆቃ ያመራል/ያስገባል። የሀገራችን የመከራ ገመድ መበጠሱ ቀርቶ፥ ወደ አልታሰበ የባርነት

*ጥብቅ ሰንሰለትነት ይለወጣል፡፡ ከኢትዮጵያ የታወቁና የለየላቸው ጠላቶች በስተቀር ይህን የሚመኝ ዜጋ አይኖርም፡፡*

*ሀገራችን ኢትዮጵያና ዜጎቿ የአምባገነኖች ሥርዓትና ጭቆና ሊፈራረቁባቸው ይገባቸዋል የተባሉ ይመስል ብሎም፥ ጭቆና፥ ረሀብና ዕርዛት፥ ስደትና እስራት፥ በሽታና ድህነት ጦርነትና ዕልቂት ለእነርሱ ብቻ የተሰጠ ዕድል ፋንታ እንደሆነ ተቆጥሮና የራሳቸው ጉዳይ ነው ተብለው ካልተፈረደባቸው በስተቀር፥ ከዚህ ተፈራራቂ አዙሪት መውጣት ይገባቸዋል፡፡ ይህ ተስፋ ደግሞ በወያኔ የዘረኞች ሥርዓት የሚከሰት አይሆንም፡፡ የወያኔን ሥርዓት እየጠጋገንን የተሻለ ሁኔታን ማምጣት እንችላለን የሚሉ ክፍሎች ከማነኛው በፊት የሚያታልሉት እነርሱን እራሳቸውን እንጅ ማንንም አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ የአዞ እንባ የሚያለቅስለትንና የዘለቄታ ጥቅሙን የሚያስጠብቅለትን ዕውነተኛ ታጋይ በሚገባ ለማወቅ የሚያስችለው ተመክሮና ዕውቀት አለው፡፡*

*ኢትዮጵያ በዓለም ካሉ ሀገሮች ውስጥ በሁለንተናዊ መስፈርቶች ስትገመገም፥ በኋላ ቀርነት ከተፈረጁት ሀገራት መካከል የመጀሪያውን ረድፍ ይዛለች፡፡ ለም መሬት፥ ታላላቅ ወንዞች፥ ተስማሚ የአየር ጠባያትና በዕርሻ ተግባር የተሰማራ ብርቱ ገበሬ ያላት ሀገር፥ ዜጎቿን እንኳ መመገብ ተስኗታል፡፡ በዓለም ገፅ የተወገደው ፈንጣጣ እንኳን ሳይቀር፥ እንዳይጠፋ በቅርስነት መቀመጥ አለበት የተባለ ይመስል የሚገኘው በእኛው ሀገር ብቻ ሆኗል፡፡ ከዚህም በቀር የተለያዩ የበሽታ ዓይነቶች በብዛት ነዋሪዎቿን በመቅጠፍ ላይ ናቸው፡፡ የሥራ አጡ ብዛትና የኑሮው ውድነት ሰማይ-ጠቀስ መሆን፥ በጠቅላላው የፖለቲካው ምስቅልቅልነት፥ የኢኮኖሚው ድቀትና የማኅበራዊ ኑሮውን ቀውስ ስንገመግም፥ ወደፊት ይህን ውስብስብ ችግር ለመፍታት ኃላፊነት የሚሸከመውን ኃይል ጥናቱን ይስጠው ተብሎ ሊታዘንለት የሚገባ እንጅ፥ ሥልጣን መያዝ አለብኝ ተብሎ፥ የሚራኮቱበት ክስተት ሊሆን አይችልም፡፡ የሀገራችን ዘርፈ- ብዙና ውስብስብ ችግሮችን በዚህ በእኛ ልሳን ዘርዝሮ ለመጨረስ ይቻላል ብሎ መሞከር አግባብነት የሌለው ብቻ ሳይሆን፥ ጥረቱ የችግሩን ክብደት ሊያሳንሰው ይችላል ብለን እንሰጋለን፡፡ ዕውነት መናገር ግዴታ ነውና፥ችግራችን እጅግ ውስብስብ በመሆኑ ወያኔን በማስወገድ ብቻ የሚያከትም አይሆንም፡፡ ኤኮኖሚውን ምስቅልቅል፥ ሀገሪቱን ፍርክስክስ፥ ዘጎቿን ብትንትን፥ ትውልዱን ጥፍጥፍት፥ ባህሏን ርክስክስ፥ ታሪኳን ብልሽልሽት አድሮጎ ለማጥፋት የሚጣደፈው የወያኔ ዘረኛ ቡድን ሀገሪቱን ድምጥማጧን አጥፍቶ፥ የመጨረሻውን ምዕራፍ ለመደምደም መዘጋጀቱን አለመረዳት፥ ሀገሪቱን አጥፍቶ ከሚጠፋው ከራሱ ከወያኔ ተለይቶ የሚታይ ሊሆን አይችልም፡፡ ወንጀል መፈፀሙን እያየ-እየሰማ የወንጀሉን ድርጊት አለማወገዝ ወንጀሉም እንዳይፈፀም አለመከላከል፥ ወንጀሉን ከሚፈፅሙት ክፍሎች ጋር አብሮ ያስከስሰዋል፡፡ ከዚህ ሁሉ ጣጣ ነፃ መውጣት የሚቻለው፥ ሀገራችንን ራዕይ ባለው የትግል አድማስ አስግብቶ ከዘረኞች አምባገነን አገዛዝ ማላቀቅ ብቻ ነው፡፡ ራዕይ ስንል ሁለት የትግል ሂደቶችን በግምት በማስገባት የፕሮግራም ቅደም ተከተሎችን ከሕዝቡ ተሳትፎ ጋር አዋህዶ ለመሠረታዊ የዴሞክራሲ ግንባታ ላይ መረባረብ ያስፈልጋል ማለታችን ነው፡፡*

*በአሁኑ ወቅት የተቃዋሚ ድርጅቶች ትግል፥ በምስቅልቅል ፖለቲካ ውስጥ ገብቶ፥ አቅጣጫና የቅደም ተከተል ሂደት አጥቶ፥ ወዴት መሄድ እንዳለበትና ምንስ ማድረግ እንደሚኖርበት መገንዘብ አቅቶት እንዲያው የዳበሳ ጉዞ ለማድረግ በሚያስችለው ሁኔታ ላይ እንዳለ የሚገነዘበው መሆኑን እንኳ የተረዳው አይደለም፡፡ አንዳንዶቹማ እንዲያውም የተቃዋሚነት ባኅርያቸው እየወየበባቸው ከመሄዱ የተነሳ፥ የመለስ ዜናዊን ጥሪ ለመቀበል በመጠባበቅ ላይ እንደሚገኙ የአደባባይ ምሥጢር ሆኗል፡፡ ይኸም ለሚቀጥለው የወያኔ ምርጫ ለመሳተፍ የሚያስችል ቅድመ-ዝግጅት ለማድረግና የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት የሚታገሉትንና በወያኔ ላይ የማያወላውል አቋም ያላቸውን ኃይሎች ለመጉዳት፥ ብሎም የሕዝቡን መራራ ትግል አቅጣጫ ለማሳት የሚደረግ ተጨፈኑና ላታልላችሁ የሚል ርካሽና ቢከፍቱት ተልባ የሆነ ደካማነት ነው፡፡ ይህም ለእኛ አሳፋሪና በተሰውት እልፍ አዕላፍ*

ሰማዕታት ክቡር ደም መቀለድና ታሪካዊ አፅማቸውንም ማርክስ ይሆናል፡፡ ከሠላሳ አምስት ዓመታት መራራ ትግል በኋላና ብሎም፥ ያ ሁሉ መስዋዕት ተከፍሎ፥ ለጥገናዊ ለውጥ ደፋ ቀና ማለት፥ የቆሙለትንና የተሰውለትን ዓላማ መካድ ብቻ ሳይሆን፥ ድርጊቱ፥ አሳፋሪና በታሪክም የሚያስወቅስ ነው፡፡

ኢሕአፓ፥ሀገራችን የወደቀችበትን አደገኛ ሁኔታ በመገንዘብና በራስ አነሳሽነት ኢትዮጵያን ለማዳን የሚቻለው ትግል ተፋፍሞ ማስወገድ መሆኑን አስቀድሞ በመረዳት፥ ትላንት ሲያጠፉት ከነበሩ ክፍሎች ጋር ሕብረት በመፍጠር የትግሉ አቅጣጫ ሀገሪቱን ለማዳን በሚደረገው ሂደት ላይ እንዲተኮር አደረገ፡፡ በዚህ ሂደት ለኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግልና መልከዐ-ምድር አዲስ ክስተት እንዲፈጠር ሆነ፡፡ በኢትዮጵያ መዳን የሚያምነው ዜጋ ሁሉ ከደስታው የተነሳ ሙሉ ትብብሩንና ድጋፉን አሳየ፡፡ ምንም እንኳን የየድርጅቶቹ ዓቅምና ይዘት በጣም የተለያየ ቢሆንም ይህ መልካም ጅማሮም እስከ ተወሰነ ምዕራፍ ሁሉን በማስተባበር ለመጓዝ ችሏል፡፡ ይህ መልካም ጅማሮ በተለያዩ ምክንያቶች እንዲሰናከል ከተደረገ በኋላ ፥ ዛሬ ከሠላሳ አምስት ዓመት በፊት ወደ ነበረው ሁኔታ ለመለወጥና ለዳግም ምፅዓተ- ፅልምት ለመመለስ ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡ ይህ መጥፎ አዝማሚያ ሊፈጥር የሚችለውን አደገኛ ሁኔታና የሚያስከትለውንም መቆሚያና መቆጣጠሪያ የማይገኝለት ጥፋት አስቀድሞ አለመገመት እጅግ ኃላፊነት የጎደለውና በጥላቻ ተፀንሶ የጥላቻ መርዝ የሚተፋ የጥፋት በር ከፋች ነው፡፡ ልክ የዛሬ ሠላሳ አምስት ዓመት የተደረገውን ጥፋት በሌላ ሁኔታና አጋጣሚ እንዲከሰት በማድረግ፥ ያ ሕዝብ እንደገና ወደ ሌላ የደም አለባ እንዲዘፈቅ በሚደረገው ዝግጅት፥ እኛ ኢሕአፓዎች ተካፋይ ለመሆን ዝግጁ አይደለንም፡፡ እንዳይመጣም እንከላከላለን፡፡ እንቃወማለንም፡፡ ይህንን ጥፋት ለመከላከል የሚቻለው ደግሞ ፥ ፀንቶ በመቆም የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት በፅናት የሚታገሉት ወያኔን እየተፋለሙ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ የመብቱና የነፃነቱ ባለቤት ለማድረግ የሚያስችለውን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲመሰርቱ ብቻ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ እውን ሊሆን የሚችለው ግን በብሔራዊ ራዕይ ላይ የተመሠረተ፥ የሀገራችንን ሁለንተናዊ ችግሮችን በሂደት ሊያስወግድ የሚችል ሀገራዊ ፕሮግራም የነደፈና ከሁሉም በላይ ደግሞ ሁሉንም የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ሊያካትት በሚችል ሂደትና ሁለገብ ትግል ተካሂዶ በፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ላይ የማያዳግም ድልን ሲጎናፀፉ ብቻ ነው፡፡ ይህንን እውን ለማድረግ ፍላጎቱም፥ ቁርጠኝነቱም፥ ፅናቱም፥ የሕዝብና የሀገር ታማኝነቱም ሆነ ቆራጥነቱ ሊመጣ የሚችለው ለሥርዓት ለውጥ ለማምጣት ከሚታገሉ ኃይሎች ዘንድ ብቻ ነው ብለን እናምናለን፡፡

ከአንድ አምባገነን ሥርዓት ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመረማመድ፥ የሽግግር ወቅት አስፈላጊነት የግድ ነው፡፡ይህንን በሚመለከት ኢሕአፓ ከዓመታት በፊት በጥናት የተደገፈ ሰነድ በማዘጋጀት ለሕዝብ ይፋ አድርጓል፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ስር የሰደደና የደለበ ችግር ያላትን ሀገር፥ በጦርነት ዕልቂት የደቀቀ ዜጋ የሞላባትን ሀገር፥ ከሁሉም በላይ ደግሞ፥ የወያኔ ጎጠኛ አገዛዝ የነሰነሰውን የዘረኝነት መርዝ ነቃቅሎ ለመጣል፥ በግድ ሰላማዊ የሽግግር ወቅት መኖር አለበት ብሎ ኢሕአፓ ከልብ ያምንበታል፡፡ የሀገራችን ችግሮች የሚፈቱት በሰከነና እንደ ችግሮቹ መጠንና ክብደት በሂደት እየተቀረፉ ሲሄዱ እንጅ፥ ለፖለቲካ ሥልጣን በሚቋምጡ ዛሬ ብልጭ ብለው ነገ በሚከስሙ ግለሰቦችና ግብታዊ ተግባራቸው አይደለም፡፡ ዘላቂ መፍትኄ ሊገኝ የሚችለውም፥ የሀገሪቱ ችግር ሁለንተናዊ ገፅታ ባለው መልኩ ባካተተ ዕይታ ሲገመገም ነው፡፡ በይድረስ ይድረስ መፍትኄ የሀገራችን ሁለንተናዊ ችግሮች ይፈታሉ ብለን አናምንም፡፡ ለዚህም ነው የሽግግር ወቅት አስፈላጊ ነው የምንለው፡፡ የሽግግሩ ወቅት ለዘለቄታው የዴሞክራሲ ሥርዓት ምሥረታ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት ዛሬ በዴሞክራሲ ሥርዓት የበለፀገ ተመክሮ ካካበቱ ሀገሮች መቅሰም ይቻላል፡፡ የአፄውን ሥርዓት፥ በወታደር አምባገነን ቡድን፥ የደርግን ፋሽስታዊ አገዛዝ ደግሞ በወያኔ ዘረኛ ሥርዓት ማፈራረቁ ምን ያህል መራራ ተመክሮ እንዳስገበየለት የኢትዮጵያ ሕዝብ መሪር ትዝታውና ቁጭቱ ነው፡፡ ይህ ወደ ፊት እንዲደገም የሕዝባችን ፍላጎትና ምኞት አይደለም፡፡ ከተፈራራቂ የአምባገነን ሥርዓት ሀገሪቱን ለማላቀቅ፥ አስቀድሞ ለአዲስ አምባገነን መምጣት ምክንያትና ሰበብ የሚሆኑትን አረሞች አስቀድሞ

ማክሰምና እንዳይበቅሉም የኢትዮጵያን የፖለቲካ ትግል ማሳዎች ከተባዮች ማጽዳት ይገባል፡፡

በአሁኑ ወቅት በሥልጣን ላይ ያለው ዘረኛው አምባገነን ሥርዓት በሁለንተናዊ ገፅታው በችግር የተወጠረና ዙሪያውም በልዩ ልዩ አደጋዎች የተከበበ ሆኗል፡፡ በሶማሊያ የአንድ ልዕለ-ኃያልን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል በተሰጠው መመሪያና ትዕዛዝ በማያገባው ገብቶ በሶማሊያ ውስጥ ባደረገው የጀብደኝነት ሥራ እስከ አንገቱ ተዘፍቆ ሊወጣ አልቻለም፡፡ የብዙ ወታደሮችን ህይወት ለመቅጠፍ ምክንያት በሆነው ጦርነት ውስጥ በመግባት በሚሊዮን የሚቆጠር የሀገራችንን ሀብት በማባከን ላይ ይገኛል፡፡ በሽህ ለሚቆጠሩ ሰላማዊ ሰዎች መገደል ምክንያት ሆኗል፡፡ ወያኔ በሶማሊያ ከተዘፈቀበት ማጥ ለመውጣት አልተቻለውም፡፡ ወደፊት ከሶማሊያ ጋር በሰላም ለመኖር የሚያስችል የመልካም ጉርብትና መሠረቶችንም አበላሽቶታል፡፡ ጠንቁም ለትውልድ የሚተላለፍ መርዝ ይሆናል፡፡ የወያኔ የሶማሊያ ፖሊሲ፥ በሽብርና በጦርነት ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ፥ ሰበቡ በኦጋዴን ያለውን ሁኔታ ውስብስብና አደገኛ አድርጎታል፡፡ መፍትኄ ለመፈለግ የሚያስችል ዕድል ሁሉ እየዘጋው ነው፡፡ በጦርነት፥ በሽብርና በቀውስ ላይ የተመሠረተ ፖሊሲ ደግሞ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት ጭራሽ አያመጣም፡፡ ለጥፋትና ለማያባራ ጦርነት ግን ሁሉን ነገር የሚያመቻች ይሆናል፡፡ በሰሜን በኩል ያለው ሁኔታም እንደዚሁ ወያኔ በፈጠረው መሠረታዊ ችግር ምክንያት የአካባቢውን ዜጎች በተቀበረ ፈንጅ ውስጥ ታጥረው እንዲኖሩ አድርጓቸዋል፡፡ ዘለዓለም በታሪካቸው በሰላምና በመተባበር የኖሩትን ዜጎች በመጠራጠር፥ በመፈራራትና በመጠላላት እንዲተያዩ አድርጓቸዋል፡፡ ይህም ሁኔታ፥ በማንኛውም ወቅት ሊፈነዳ በሚችል የአውዳሚ ጦርነትና የዕልቂት ዳመና እንዲያንዣብበት አድርጎታል፡፡ በመሆኑም ነዋሪዎቹ ሰላምና መረጋጋት አግኝተው፥ ፍትህ-ርትዕን አስፍነው፥ ወደ ዋናውና የጋራ ችግራቸው ማለትም፥ ረሀብን፥ ድህነትና በሽታን፥ ኃላቀርነትን ለማስወገድ በሚያስችላቸው ሂደት እንዳያተኩሩ አድርጓቸዋል፡፡ አምባገነኖች፥የሚገዙት ሕዝብ ከጭቆና አገዛዛቸው ነፃ ለመውጣት በሚያደርገው እንቅስቃሴ የትኩረት አቅጣጫውን ለማሳትና ለማወናበድ በግድ ሁከትና ሽብር መፍጠር አስፈላጊያቸው ነው፡፡ የወያኔ መሪዎችም ይህንን ቢያደርጉ የሚያስገርም ሊሆን አይችልም፡፡ የሀገራችንንም የሰሜኑን ክፍል በማያቋርጥ ሽብርና የጦርነት ዳመና ስር እንዲኖር ማድረጋቸው ታዲያ ለማንም ስውር አይሆንም፡፡ በኢትዮጵያ ምዕራባዊ ክፍላተ ሀገር የተፈጠረውም መሬትን ለባዕድ አሳልፎ የመስጠቱ ሁኔታ የወያኔ መሪዎች ኢትዮጵያን ለማጥፋት ከሚያደርጉት ታላቅ ሴራና ወንጀል ተለይቶ የሚታይ አይደለም፡፡ የኢትዮጵያን ሰፊና፥ ለም መሬት ለሱዳኖች ማስረከብ፥ የወያኔ የረዥም ጊዜ ዓላማና ዕቅድ ስለነበር፥ እንደ አዲስ ክስተት የሚታይ አይደለም፡፡ ያም ሆኖ ግን፥ ጠቅላላ የሀገሪቱን ሆኔታ እያባባሰው ወደተዳፈነው እሳተ-ገሞራ ፍንዳታ ያሸጋግረዋል እንጅ ጭራሽ የተሻለ ሁኔታን ለወያኔ አያመጣለትም፡፡ የወያኔ መሪዎች በሀገራችን ልዩ ልዩ አቅጣጫዎች የሚፈጥሩትን ሁከትና ሽብር ምክንያት በማድረግ፥ ጠቅላላ ሀገራዊ ቀውስ በማምጣት ከተቃጣባቸው ሕዝባዊ አመፅ ለመዳን ጊዜያዊ እፎይታን የሚያገኙ ይመስላቸዋል፡፡ ይህ ጊዜው ያለፈበት የአምባገነን ዘዴ፥ ያረጀ-ያፈጀ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁን የደረሰበትን ንቃተ-ኅሊና አለመገንዘብና የዓለምንም ሁኔታ በቅጡ አለመረዳት ነው፡፡

ያም ሆኖ ግን በአንድ ነገር ብቻ ሁሉም ሊስማማ የሚችልበት ነባራዊ ሁኔታ መኖሩን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ይኸውም የወያኔን መሪዎች የልብ ልብ የሰጣቸው፥ በዘላቂ ራዕይ ላይ የተመሠረተ የተቃዋሚ ኃይሎች ጠንካራ እንቅስቃሴ አለመኖሩ ብቻ ነው፡፡ ከማንም በላይ ይህንን ሐቅ የተረዱት ደግሞ፥ የወያኔ የበላይ ጠባቂዎችና ሌሎች የሀገራችን ጠላቶች ናቸው፡፡ ሀገራችንን ከውስጥና ከውጭ ጠላቶቿ ለማዳን፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚኖሩት ምርጫዎች ሁለት ብቻ ናቸው፡፡ አንደኛውና ቅድሚያም ሊሰጠው የሚገባው፥ የወያኔን ዘረኛ አገዛዝ ተፃርረው የቆሙ፥ ብሎም በኢትዮጵያ ስር ነቀል የሆነ የሥርዓት ለውጥ መምጣት አለበት ብለው ከልብ ያመኑ ተቃዋሚ ኃይሎች በዕምነታቸው ላይ የተመሰረተ ጠንካራ ኅብረት በመፍጠር ዘረኛውን ሥርዓት ገርስሶ በዴሞክራሲ ሥርዓት መተካት ነው፡፡

ይህ ዕውን እንዲሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ በነቂስ በድርጅቶቹ ላይ ጠንካራ ተፅዕኖና ያልተቋረጠ ግፊት ማድረግ ይኖርበታል። ከሕዝብ የሚደበቅ አንዳችም ነገር ስለማይኖር፤ በድርጅቶቹ መካከል ማን አጥፊ ማን አልሚ መሆኑን እየተረዳ ሕዝቡ የራሱን ፍርድና ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል። የጅምላ ፍርድና ውሳኔ መፍትኄ አላመጣም ። እስካሁን! የኢትዮጵያን ሕዝብ ሙሉ ትብብርና ድጋፍ፥ ያልተቋረጠ ተሳትፎና ትክክለኛ ፍርድና ብያኔን ያላገኘ ትግል ውጤት አያመጣም። ሁለተኛውና የመጨረሻው አማራጭ፥ የኢትዮጵያ ጠቅላላና ሕዝባዊ አመፅ ነው። ክተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት ብሎ በገጠርም በከተማም ለማይቀረው መሥዋዕት ተዘጋጅቶ የወያኔን አገዛዝ መፋለምና ማሸነፍ ነው። ይህም የሁሉንም ዜጋ ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ እንደመሆኑ ዜጎች በሙሉ የሚጠቃለሉበት የትግል አዋጅ፤ ዕቅድና ዝግጅት ሊኖር ግድ ይላል። በድንቁርና ላይ የተመሰረተውን የወያኔን ዕብጠት ማስተንፈስ የሚቻለውም በዚህ ዓይነት የትግል ስልት ብቻ መሆኑን ከምን ጊዜውም በበለጠ በአሁን ወቅት መገንዘብ አስፈላጊ ነው። በዕርግጥ ለጥገናዊ ለውጥ ብቻ የተዘጋጁ ክፍሎች ካለሆኑ በስተቀር ! ይዚህ ዓይነት ትግል አንድ ጊዜ ከተጀመረ፥ እንደ ሰደድ እሳት እየተቀጣጠለ በመሄድ ወያኔን ከነ መርዘኛ/ ዘረኛ ሥርዓቱ ዶግአመድ እንደሚያደርገው የታሪክ ሐቅ ነው። የዚህኛው የትግል አማራጭ፥ ብሔራዊ መልክና ሕዝባዊ ይዘት መኖሩን ካረጋገጡ፥ የወያኔ የበላይ ጠባቂዎችና ምዕራባውያን አሽቃባጮቹ ፥ ሁሉንም በሚያስገርም ፍጥነት ወያኔን ከድተውና አጋፍጠው፥ አቸናፊነቱ ከተረጋገጠው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ጎን እንደሚቆሙ ያለፈው ተለዋዋጭ ታሪካቸው አረጋግጦ ያመስዘገበው ሐቅ ነው። ምክንያቱም የእነርሱ ቋሚና የማይለወጥ ፖሊሲያቸው የተመሠረተው፥ በቋሚ ወዳጅነት ወይም ጠላትነት ላይ ሳይሆን፥ የዘላቂ ጥቅማቸውን በማስጠበቅ ላይ ብቻ በመሆኑ ነው። ታዲያ እኛም የሀገራችንን ዘላቂና ዘለዓለማዊ ብሔራዊ ጥቅማችንን ዋስትና ባለው መልኩ እያስጠበቅን ልናስከብር የምንችለው፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘላቂና ቋሚ ጥቅም ላይ በተመሠረተ ፅኑ ፖሊሲ መሆኑን ልንጠራጠር አይገባንም። በዚህ ተለዋዋጭና ተገለባባጭ በሆነው የዓለም ፖለቲካና ዓለምአቀፍ ዲፕሎማሲ፥ ማመን የምንችለው እራሳችን፥ መተማመን የሚገባንም የራሳችን ብሔራዊ ጥቅም ሊያስከብርልን በሚያስችለን በራሳችን ሀብት፥ ዕውቀት፥ ጉልበት፥ ኃይል፥ አንድነትና ትብብር ብቻ ነው። እራሳችንን አክብረን ሌሎቹም ሊያከብሩን የሚችሉት በራስ መተማመን ላይ በተመሠረተ የውስጥና የውጭ ፖሊሲያችን ነው። ከሰባ ሚሊዮን በላይ ያላት ሀገራችን፥ ያልተነካ የተፈጥሮ ሃብቷን፥ በከርሰ ምድር የተከማቸውን ማዕደኗንና የሠለጠነ የሰው ኃይሏንና ጉልበቷን አስተባብራ ከሰራች፥ በአጭር ጊዜ ውስጥ የዕድገት ዕመርታ በማሳየት ታምራዊ ለውጥ የማታስመዘግብበት ምክንያት አይኖርም። ለዚህ ሁሉ ዋስትናው ደግሞ የሀገሪቱን ዜጎች በሙሉ ሊያሳትፍ የሚችል የዴሞክራሲ ሥርዓት መመስረቱ ነው። ይህን ለማስገኘት በግድ ብሄራዊ ራዕይ ያላቸው ብቁ ድርጅቶችና መሪዎች መኖራቸው ወሳኝ ነው። ብሔራዊ ራዕይ ከሌለ ወደየት አቅጣጫ ለመሄድ እንኳ አስቸጋሪ ነው። ዳግም ራዕይ ስንል ራዕይ ሲሉ ብለን በሰፊው መዘርዘር ባያስፈልገንም ለእኛ ራዕይ ማለት ለግል ዝ ሹመት፤ የአድርባይነትን ፍላጎት ለማሟላትና ለባለነፍጥ ገዢ ሁሉ ሰግዶና ተጎንብሶ የሚገኝን ጥቅም ብቻ የሚያይ የሚያቅፍ ሊሆን አይችልም። ህዝባዊ ራዕይ ነው ራዕያችን--ሕዝብና ሀገርን ያስቀደመ። በመሆኑም ነገ ከምንመኘው ግባችን ለመድረስ ዛሬ በሕዝባዊ ራዕይ ላይ የተመሰረተ ትግል ማካሄድ መቻላችን ወሳኝ ነው።

ኢሕአፓ ለዘለዓለማዊት ኢትዮጵያ እየታገለ ይሰዋል፥
እየተሰዋም ህልውናዋን ያስጠብቃል ! ያስከብራል !